**International Ethiopian Woman Organization IEWO**

**ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ)**

**IEWO, 1515 South 4th street #1801, Minneapolis, MN 55454, USA**

# ጉል ጠላት እያለ!

እንደሚታወቀው ሁሉ ማንኛውም የህብረተሰብ አባላት የራሳቸውን ዜጋና ባህል ከሌሎች ማለትም ከነሱ ልዩ ከሆኑት የተሻለ ክብደትና ተወዳጅነት እንዲሁም በላጭነት እንዳለው ከፍተኛ ዕምነት ያላቸው እንደሆነ በሰፊው ይነግራል ብዙም ተፅፎበታል። የእንግሊዘኛ ተናጋር የሆኑት ፈረንጆች ኤትኖሴንተርዘም (Ethnocentrism) የሚሉት ነው። ይህም የሚያሳየን የራስ የሆነን ነገርና ባህልን መውደድ ማክበር ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ሲያሳየን በብዙ አገሮች ግን የሚያምኑበትና ለብዙ ጊዜ ይዘውት የቆዩት ባህል ጉጂነት ጉልቶ ከታያቸው ሊጋደሉትና በሌላ ባህላዊ አስተሳሰብ ለመተካት ይወስናሉ።

የኛ የኢትዮድያውያን ባህልና የባህል ዘርፎች ውስብስብ ያሉ ክብደት ያላቸው መሆናቸው በሰፊው ከመነገሩም አልፎ ኢትዮድያውያን የሆን በሙሉ በስሜት እንኮራባቸዋለን። ለባህላችን ቀጣይነትና ክብረት ሲባል ህይወታቸውን ለመሰዋት ፈቃደኛ የሆኑ የሐገር ዜጐች አሉ ቢባል ስህተት አይሆንም።

በአጠቃላይ የባህላችን ታላቅነት አኩሪነት በብዙዎቻችን ስሜት ውስጥ ጠንካራ ቢሆንም ጉጂነታቸው ከፍተኛ ሆነው የሚታዩንና ለአብሮ መኖራችን ዋስትና ከፍተኛ መሰናክልና ምንጭ ናቸው ብለን የምናምንባቸውን ለማወቅም ሆነ ለመዋጋት እስካሁን ፈቃደኞች ሆነን አልተገኘንም።

በጉጂናነታቸው ጉልተው ከሚታዩት ለምሳሌ ለመጥቀስም ያህል በኢትዮድያውያን ላይ ብዙ ጊዜ በዕምነት ምትክ ተጠራጣሪነት መስፈን፣ ሁሉንም አጥፊ ብልጣብልጥነት፣ ስርሰደድ የሆነ የማይታረቅ ቂም ያዢነት፣ የጋራ ችግርን የግል አርጐ መመልከት ከፍተኛ የቡድን አማኝነት እና የመሳሰሉት ይገኙበታ።

የውጪ ታዛቢዎችም ሆኑ ኢትዮድያውያን የሚጋሯቸው ከባህላችን የዘርፍ ምልክቶች ጨምረን ለመጥቀስም እኛ ኢትዮድያውያን በአንድነት መብላት፣ ሃዘንም ሆነ ደስታን አብሮ መካፈል የሚሉት ይገኙበታል። ይህም የሚያመለክተን የሃይማኖት ሊቃውነቶችና አስተማሪዎች በሃገር አንድነት ጥረት ሲያረጉ ከነበሩት መሪዎች የበለጠ ተፅእኖ እንደነበራችው ነው።

የድርጅቶች ከቀን ወደ ቀን መበታተን፥ ተግባብቶ አንድነት ፈጥሮ መስራት አለመቻል ምክንያትና የሃገራችን ሕዝብ በብዙ አቅጣጫ ከሚያስቃየው ችግር የበለጠ ጠላታችን ጉጂ የባህላችን ዘርፎች የአስተሳሰባችን ቀያሾች የሆኑት ናቸው ብለው የሚያምኑት ዶክተር ማሩ ጉበና **"ጉል ጠላት እያለ"** በሚል ርዕስ እንደ መንደርደሪያ በማድረግ ያውያዩናል።

- **ቀኑ የፊታችን ቅዳሜ November 14th ሰዓት 4 AM Eastern Time USA, 16:00 hours Europe.**
- **ቦታ ዓለምዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ፓልቶክ መወያያ መድረክ (International Ethiopian Women's Organization Paltalk Forum)**

**ዓለምዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ፓልቶክ ፎሩም ሲሆን በመወያያ መድረካችን እንድትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ተጋብዛችኋል**

**ዓለምዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት**

[www.aesed.org](http://www.aesed.org)

[aesed.iewo@gmail.com](mailto:aesed.iewo@gmail.com)